ይህ አዋጅ "ለድሬጃራ የመጠጥ ዉሃ ፕሮጀክት ክፊል ማስፈፀሚያ በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና ከሴክተር መ/ቤቶች ፣ ከህዝባዊ ድርጅቶች ብድር ለማግኘት የተፈፀመዉን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር 29/1994 " ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ዉስጥ

ሀ/ "የብድር ስምምነት" ማለት በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እና በሴክተር መ/ቤቶች ፣ በህዝባዊ ድርጅቶች መካከል በጥር 22 ቀን 1994 ዓ/ም በሐረር ከተማ የተፈፀመዉ ሐረ1/ከድጃ ቁጥር 01 እስከ 07/ የብድር ስምምነት ነዉ፡፡

ለ/ "ሴክተር መስሪያ ቤቶች" ማለት በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥር የተደራጁት የትምህርት ቢሮ፣ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ኢንቨስትመንት ጽ/ቤት፣ ሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤትና የፋይናንስ ቢሮ ናቸዉ፡፡

ሐ/ "ህዝባዊ ድርጅቶች" ማለት በሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥር፣ በራሳቸዉ በጀት የሚተዳደሩ መንግስታዊ መዋቅር ያላቸዉ አካላት ሲሆኑ እነሱም የዉሃና ፍሳሽ ባለሥልጣንና የሐረር ከተማ ማዘጋጃ ቤት ናቸዉ፡፡

## 3. የፋይናንስ ቢሮ ሥልጣን

የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፋይናንስ ቢሮ በብድር ስምምነቱ የተገኘዉን ብር 8,197,000.00 /ስምንት ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና ሰባት ሺ ብር/ በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲዉል ለማድረግ በዚህ አዋጅ እና በቢሮዉ ማቋቋሚያ አዋጅ 2/1988 አንቀጽ 13/6 መሠረት ይህ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## 4. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥር 23 ቀን 1994 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*ሐረር ጥር 23/1994 ዓ/ም*

*አቶ ፋአድ ኢብራሂም*

*የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ*

*መንግስት ፕሬዝዳንት*